<u>ርዕሰ አንቀፅ</u>

# መድበለ-ባህል፤ አንድ ሀገር!
# (Multicultural, One country)

መቸም ተወልደው እትብት የጣሉባትና ሀረግ የሚስቡባት ምድረ-ሀገር ፤ ለእያንዳንዱ ሰው የተለየ ፍቅርና ክብር አላት። ልክ ዘጠኝ ወር አርግዛና አምጣ እንደወለደች እናት ፤ ዘር ማንዘር የበቀለባትና ልዩ ባህርይ ያጎናጸፈች ሀገርም ፤ ለእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል የእርሱ/እርሱዋ (የእነርሱ) ሀገርና ባህል ፤ ከሌላው ሀገር እንደው ምናልባት በልጣ ባትታይም ፤ ያነሰች ነች ብሎ ማመን ግን እምብኝ ይላል። ይህ በመሰረቱ ራስን የመጠበቅና «የፍቅር ጉዳይ» ነውና ፤ ቢበረታታ እንጅ ክፉ ነው አይባልም። መጥፎ የሚሆነው ወዳጅንና ጠላትን ያለየ «እውር ፍቅር» ሲሆን ፤ ወይም ደግሞ የእሱነቱን ምንጭ ለመከላከልና ለመጠበቅ ሲባል ፤ «ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ» አይነት «ጠርገህ በለው» የሚል አመለካከት ሲቀነቀንና በተግባር ላይም ሲውል ነው።

አሸባሪነት በእውነተኛ ትርጉሙ የሚደገፍ አይደለም። በአንድ የህብረተሰብ ክፍል ላይ በደልና ግፍ በሚፈጸምበት ወቅትና ፤ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል መድረኩ በአምባገነኖች ተዘግቶ በደሉ ሲቀጥል ፤ ዘላቂ ፍትህን ለማግኘት ከአመባገነኖች ጋር የሚደረግ ራስን የመከላከል ትግል «ሀጋዊነት» እንዳለው ይታመናል። ነገር ግን ፤ ሁኔ ታው ሳያስገድድ ተሰሚነትን ለመፍጠር ተብሎም ሆነ ፤ በፖለቲካው መስክ ትንሽ ነጥብ ለማስመዝገብ ሲባል ፤ በብዙሃኑ ደህንነትና የእለት ተእልት ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ሊያመጣ የሚችል የእውር ድንብስ እርምጃ መውሰድ ከታሰበ ፤ አላማ የለሽነት ብቻ ሳይሆን ትርጉም የሌለው ጭካኔም ይሆናል። ጋዜጣችን ሐዋርያ ለሰው ልጆች መብት መከበር ፤ ለፍትህ ርትእ መስፈን ፤ ከተበደሉት ብዙሃን ጎን ቆማ የበኩሉዋን አስተዋጽኦ ማድረጉዋን ትቀጥላለች። ዳሩ ግን ፤ አግባብነት በሌለው መንገድ በሰላማዊው ህዝብ ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እርምጃ ካለ ነውር ነው ለማለት እንገደዳለን። ይህን ማንሳታችን በቅርቡ በካናዳችን ውስጥም ቶሮንቶ አካባቢ ተከስቶ በተለያዩ የብዙሃን መገናኛዎች ሲስተጋባ የሰነበተውን የ17 ግለሰቦች በአሸባሪነት ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የመዋልን ጉዳይ አመልካች ነው። በቁጥጥር ሥር የዋሉት ወገኖች ወንጀለኞች አይደሉም ወይም ናቸው ለማለት ግን አይደለም ፣ ያ የፍርድ ቤት ጉዳይ ነውና።

ካናዳ በውስጡዋ ለምንገኘው ሁሉ የጋራ መኖሪያ አገራችን ነች። ከሁሉም የዓለም አቅጣጫ በተለያየ ምክንያት መጠን የሰፈርንባትና ፤ የሰላም አየር በመተንፍስ አፍርተን ፤ ወልደንና ከብደን የተከበርንባት ሀገር በመሆኑዋ ፤ ለደህንነቱዋ ልናስብና እኛ ኑዋሪዎቹዋ በቻልነው ሁሉ ዘብ ልንቆምላት እውነቱ የግድ ይለናል። ካናዳ አንድ ሀገር ብትሆንም ፤ በመድብለ-ባህል መመሪያዋ (multiculturalism) የእያንዳንዱ ማህበረሰብ ማንነት ተከብሮና ተጠብቆ በመያዙ ፤ በዓለም ላይ ካሉ ሀገሮች ልዩና የተዋበች

አድርጉታል። ይህ ልዩ መድበለ-ባህል (multicultural) ባህርይ ሊዳብርና በዘላቂነት የሁሉም መንጸባረቂያና መለያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ፥ የየግል ባህልና እምነታችን ን ፥ ለምደንና ተከብረን ከምንኖርባት የጋራ መኖሪያ ሀገራችን ጋር አዛምደን ስንይዝ ነው። ባለ ብዙ ባህሎች ፥ ግን ደግሞ የአንድ ሀገር ኑዋሪዎችና ባለአደራዎች በመሆናችን ፥ ሃላፊነትም እንዳለብን መረዳት ያስፍለጋል። ይህ ደግሞ ፥ በተለይ ለእኛ ኢትዮጵያዊ ስርዎ ላለን ካናዳዊያን ኑዋሪዎች ፥ መቻቻልና መከባበር የተለየ ተፈጥሮአዊ ባህርያችን ነው።

ከአባት እናቶቻችን የወረስነው በሃይማኖትና በባህል ተከባብሮ መኖር ፥  መርጠን በምን ኖርባቸው ሀገሮችም መልካችንና መለያችን ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል። በረጅሙ የኢትዮጵያ ሀገራችን ታሪክ ፥ ሁዋላቀር የዘውድ ሥርአቶችና አምባገነኖች ሃይማኖትን ለስልጣናቸው ማጠየቂያ እንደ የመለያያ መሳሪያ ሊጠቀሙበት ይሞክሩ እንጅ ፥ ሰፊው ህዝብ በደስታና በመከራ ሳይለያይ ፥ አብሮ ዘፍኖና አብሮ ዘምቶ ፥ አንድ የጋራ ታሪከ ገንብቶ መኖሩን ማንም አይነግረንም። አጼ ሃይለ ሥላሴ ከሚታወሱበት አንድ ነገር ፥ «ሃይማኖት የግል ፥ ሀገር የጋራ» የሚለው አገላለጻቸው መሆኑን ብዙዎች እን ደሚጠቅሱት ሁሉ ፥ በሃይማኖቶቻችን እየተከባበርን ፥ ሀገራችንና ታሪካችን በጋራ እን ከባከባለ። መብታችን ለማስጠበቅ የሌሎችን አክባሪ መሆናችን ግልጽ ቢሆንም ፥ ከእራሳችን አልፈን ከሌሎች ጋር በሃይማኖት ጉዳይ የሚያዳብለን ግዴታ የለብንም። የእኛ ኢትዮጵያዊያን ሃይማኖት (እስልምና ፥ ክርስትና ፥ ወዘተ.) ከራሳችን ባህልና ሀገራዊ ገድል ጋር የተሳሰረ ነው። የእኛ ሃይማኖት ፥ ከመንፈሳዊ እይታችን ባሻገር ፥ ኢትዮጵያዊ ባህላችን የሚንከባከብ ፥ ታሪካችን እየመረመረ የሚያርምና የሚያድስ ፥ የራሳችንን ባህርይና ስነ-ልቦና የተላበሰ ኢትዮጵያዊ ይዘትና ገጽታ ያለው እምነት ነው። በዚች በአዲሱዋ ሀገራችን በካናዳም ሆነ በሌሎች ሀገሮች የሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ና መስጊዶቻችንም አንድነትን መሰረት አድርገው የሚያስተምሩት ሰላምን ፥ ፍቅርን ፥ ተከባብሮና ተሳስቦ መኖርን እንደሚሆንና ለሌሎችም ምሳሌ  ለመሆን እንደሚያበቁን ባለሙሉ ተስፋ ነን። φ